# FY24 በጀት

## እንግሊዝኛ ተማሪዎች ግብረ ኃይል ዝመና



ናታን ኩደር፣ ዋና የፋይናንስ መኮንን
ጄሚ ራካኔሊ፣ የእቅድና ትንተና ዳይሬክተር

BOSTON Public Schools

# በቦስተን ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች ስርአት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ልጅ፣ በእያንዳንዱ ክፍል፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ታላቅ የመሆን እኩል እድል አለው

የቦስተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የእድልና የስኬት ክፍተት ፖሊሲ



# FY24 በጀት፡ ተማሪን ያማከለ ኢንቨስትመንት

**የ FY24 አጠቃላይ ፈንድ በጀት $1,439,030,665 ሲሆን ይህም የ $65 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ አለው፤ ከዚህ በታች የተገለጹትን ኢንቨስትመንቶች ጨምሮ ተማሪዎችን ለመደገፍ ቅድሚያ ከምንሰጣቸው ነገሮች ጋር መጣጣም የሚታይበት ነው።**

## ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንቶች

**$9.6ሚሊየን** ለሁሉን አቀፍ ትምህርት

**$6.3ሚሊየን** ለብዝሃ ቋንቋ ትምህርት

**$3.5ሚሊየን** ለተመጣጣኝ ማንበብና መጻፍ

**$1.2ሚሊየን** ለማህበራዊ ስራ፣ የፍትህ መገማገሚያና የአእምሮ ጤና

**$1.1ሚሊየን** ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና አማራጭ ትምህርት

**$1.9ሚሊየን** ለማህበረሰብ ተሳትፎ

**$26.0ሚሊየን ድምር**

## የተጨመሩ ወጪዎች

**$28.7ሚሊየን** ለደሞዝ

**($16.8ሚሊየን)** ለ ESSER ላይ የደመወዝ ወጪዎች

**$18.9ሚሊየን** ከፍተኛ ጥራት ላላቸው ተቋማት

**$12.3ሚሊየን** ለመጓጓዣ

**$4.8ሚሊየን** ለልዩ ትምህርት

**$0.7ሚሊየን** የዲስትሪክት ጽሕፈት ቤት የመምህራን ቅጥር፣ ለብዝሃነት፣ PD እና ድጋፍ አቅም

**$48.6ሚሊየን ድምር**

## የረጅም ጊዜ ዘላቂነት

**$15.0ሚሊየን** በ ESSER የተደገፈ አገልግሎቶችን ወደ አጠቃላይ ፈንድ ለማሸጋገር

**($24.5ሚሊየን)** ከአጠቃላይ ፈንድ ወደ ESSER ሃላፊነትን በማስተላለፍ ድጋፍን ለማዛወር

**($9.5ሚሊየን) ድምር**

# ቅድሚያ የሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት አካባቢዎች

## *የአካዳሚክ አፈጻጸምን ማስቀደምና ማፋጠን*

*ከትምህርት ቤት ኮሚቴ ጋር የተጣጣሙ ግቦች 1-5*

**$9.6ሚሊየን** አካታች የሆነ የትምህርት ስትራቴጂ፡ የፍላጎት ደረጃቸው ምንም አይነት ቢሆንም እንኳ ለሁሉም ተማሪዎች አካታች ተሞክሮዎችንና እድሎችን ማሳደግ

**$6.3ሚሊየን** የብዝሃ ቋንቋና የመድብለ ባህላል ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች፡ ውስን ወይም የተቋረጠ መደበኛ ትምህርት (SLIFE) ላላቸው ተማሪዎች ማህበራዊ ሰራተኞችን የሚያካትት ነው




**$3.5ሚሊየን** ለተመጣጣኝ ማንበብና መጻፍ

**$1.1ሚሊየን** ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና አማራጭ ትምህርት

# ቅድሚያ የሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት አካባቢዎች

## *ተገቢነት ያላቸው የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሳትፎ ተሳትፎዎችን ማዳበር*

*ከትምህርት ቤት ኮሚቴ ጋር የተጣጣመ የተማሪ ድምጽ እና የቤተሰብ ተሳትፎ እሴቶች*

**$1.9 ሚሊየት** ለቤተሰብና ለማህበረሰብ ተሳትፎ

- የተማሪዎችን የመማር ተሞክሮ እንዲሻሻል ለማድረግና የመርጃዎችን ተደራሽነት ለማገዝ አረንጓዴ አዲስ ስምምነትን ለ BPS ጨምሮ በርካታ ወረዳ አቀፍ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም በቁርጠኝነት ተነስተናል
- የቤተሰብ ተሳትፎ አመቻቾችንና የእገዛ መስመር ሃላፊዎችን ማሳደግ
- ሱፐርኢንቴንደንት ስኪፐር የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሳትፎን ወደ ምክትል ሱፐርኢንቴንደንት ደረጃ ከፍ አድርጓል

ይህ በ 114 የቤተሰብ አገናኝ ባለን የ **$8.2ሚሊየን** ዶላር ኢንቨስትመንት ላይ ይገነባል።






# የትምህርት ቤት ኮሚቴ የበጀት ችሎቶች

| | |
|---|---|
| **እሮብ፣ የካቲት 1:** | 5 ፒ.ኤም. የትምህርት ቤት ኮሚቴ ስብሰባ<br>ቅድመ-የFY24 የበጀት በዙም ይቀርባል |
| **ሐሙስ፣ የካቲት 16:** | 5 ፒ.ኤም. የጀት መስሚያ<br>የትምህርት ቤት በጀት<br>ግምገማ በዙም ይቀርባል |
| **እሮብ፣ መጋቢት 1:** | 5 ፒ.ኤም. የጀት መስሚያ<br>በማእከላዊ በጀት ላይ<br>ትኩረቱን አድርጎ በዙም<br>ይቀርባል |
| **እሮብ፣ መጋቢት 15:** | 5 ፒ.ኤም. የበጀት መስሚ<br>በምክረሃሳቡ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች በዙም<br>ምላሽ ይሰጥባቸዋል |
| **እሮብ፣ መጋቢት 22:** | FY24 በበጀት ላይ ያለ ድምጽ<br>ዙም |

# ትምህርት ቤቶች ለእንግሊዘኛ ተማሪዎች በጀት እንዴት ይመድባሉ



# የተመጣጠነ የተማሪ የገንዘብ ድጋፍ (WSF)

## የእኛ ወጥነትና ግልጽነት ያለው ቀመር በተማሪ ፍላጎትና ምዝገባ ላይ በመመርኮዝ የገንዘብ ድጋፍን እንድንለይ ያስችለናል






**<u>አጠር ያለ ፍቺ፡</u>**

“FTE” የሙሉ ጊዜ አቻን ያመለክታል

ይህ አውድ ለተማሪዎች ቡድን የተመደበውን የመምህርን የትምህርት ጊዜ (እና ስለዚህ ወጪ) መጠንን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል ነው

ለምሳሌ፡ የ 3ኛ ክፍል መምህርት ለ 1.0 FTE በክፍሏ ለሚገኙ ተማሪዎች ተመድባለች።

# የ 3 ኛ ክፍል አጠቃላይ ትምህርት ክፍል ናሙና

| | አጠቃላይ ትምህርት |
|---|---|
| በተማሪ ልክ ያለ የገንዘብ ድጋፍ | $6,539 |
| ተማሪዎች | 25 |
| የ WSF ገቢ | $163,475 |
| መምህር FTE | 1 |
| ልዩ ባለሙያ FTE | .2 |
| አማካኝ ደሞዝ | $111,009 |
| የመምህሩ ወጪ | $(133,210) |
| የክፍሉ ቀሪ | $30,265 |

**ከፍተኛው የክፍሉ መጠን = 25**



# የ 3 ኛ ክፍል አጠቃላይ ትምህርት ክፍል ናሙና

**100% ሙሉ**



**87% ሙሉ**



**50% ሙሉ**



| | 100% ሙሉ | 87% ሙሉ | 50% ሙሉ |
|---|---|---|---|
| WSF | $163,475 | $137,298 | $78,456 |
| ሰራተኛ | $133,210 | $133,210 | $133,210 |
| **ቀሪ** | **$ 30,265** | **$4,087** | **$ (54,754)** |

# የ 3ኛ ክፍል SEI ክፍል ናሙና

| | አጠቃላይ ትምህርት | SEI |
|---|---|---|
| በተማሪ ልክ ያለ የገንዘብ ድጋፍ | $6,539 | $7,745 |
| ተማሪ | 25 | 22 |
| **የ WSF ገቢ** | $163,475 | $170,390 |
| መምህር FTE | 1 | 1 |
| ልዩ ባለሙያ FTE | .2 | .2 |
| አማካኝ ደሞዝ | $111,009 | $111,009 |
| **የመምህሩ ወጪ** | $(133,210) | $(133,210) |
| **የክፍሉ ቀሪ** | **$30,265** | **37,179** |

**SEI ከፍተኛው የክፍሉ መጠን = 22**



# በአጠቃላይ ትምህርት ቅንብር ውስጥ የ ESL አገልግሎቶች

በአጠቃላይ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ ላሉ ተማሪዎች የ ESL አገልግሎቶች ወጪዎች በሚከተሉት ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡

- የቡድኖች ብዛት፡ ተማሪዎች ያለባቸ በ 2 ELD ደረጃዎች ወይም ባለ 2 ክፍል ደረጃዎች ሊመደቡ ይችላሉ።
- የሚፈለጉት የESL ትምህርት ሰአታት (ለምሳሌ ቡድን ELD 1 ተማሪዎች በቀን 2.5 ሰአት ትምህርት ያስፈልጋቸዋል)

**የተማሪዎች ብዛት በ ELD እና በክፍል**

| ELD ደረጃ | ክፍል | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | K2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2 | | | | 1 | | |
| 3 | 2 | 2 | | 1 | 1 | |
| 4 | 3 | 2 | 3 | | | 1 |

ቡድኖች A(5) B(4 ) C(3) D(2) E(1) F(1)

## ከፍተኛው የክፍሉ መጠን= 20



# በአጠቃላይ ትምህርት ቅንብር ውስጥ የ ESL አገልግሎቶች

| የተማሪዎች ብዛት በ ELD እና በክፍል | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ELD ደረጃ | ክፍል | | | | | |
| | K2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2 | | | | 1 | | |
| 3 | 2 | 2 | | 1 | 1 | |
| 4 | 3 | 2 | 3 | | | 1 |

ቡድኖች A(5) B(4) C(3) D(2) E(1) F(1)

| ELD | FTE REQ. | #ቡድኖች | FTE |
|---|---|---|---|
| 1 | 0.5 | 0 | 0 |
| 2 | 0.4 | 1 | 0.4 |
| 3 | 0.3 | 3 | 0.9 |
| 4 & 5 | 0.2 | 2 | 0.4 |
| | | FTE ድምር | 1.7 |

## ከፍተኛው የክፍሉ መጠን= 20



# በአጠቃላይ ትምህርት ቅንብር ውስጥ የ ESL አገልግሎቶች

| | ELD 1-3 | ELD 4&5 |
|---|---|---|
| በተማሪ ልክ ያለ የገንዘብ ድጋፍ | $1,207 | $302 |
| ተማሪዎች | 7 | 9 |
| **የ WSF ገቢ** | $8,449 | $2,718 |
| | | |
| ESL FTE | 1.3 | 0.4 |
| አማካኝ ደሞዝ | $111,009 | $111,009 |
| **የመምህሩ ወጪ** | $(144,312) | $(44,404) |
| | | |
| ESL ንኡስ ድምር | $(135,863) | $(41,686) |
| ESL ቀሪ | | $(177,549) |

**ከፍተኛው የክፍሉ መጠን= 20**





**ውይይት**

የዚህ አቀራረብ ጥንካሬዎች ምን ምን ነበሩ?

ድክመቶቹስ ምን ነበሩ?

በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ ማወቅ የሚፈልጉት ምንድነው?



የ BPS በድጋሚ
የሚታይ የትምህርት
ቤት የገንዘብ ድጋፍ
ፕሮጀክት

# ውጤታማ የሆነ በድጋሚ የሚታይ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ የሚከተሉትን ያደርጋል፡

1. በ BPS ተማሪዎችና በታሪክ መገለል የደረሰባቸው ቤተሰቦች ላይ ትኩረትን በማደረግ እያንዳንዱ ልጅ ውጤታማ እንዲሆንና እንዲያድግ የበለጠ ፍትሃዊ ድጋፍ ያደርጋል፣
2. ለመላ ማህበረሰባችን በግልጽ ማስቀመጥና በሚገባ እንዲረዳው ማስቻል፣
3. ለተጨማሪ ግምገማ ተገቢ ከሆነው የገንዘብ ድልድል ባሻገር ከሌሎች ሃብቶች ክፍፍል ሂደቶች ጋር ግልጽ ግንኙነቶችን ይፈጥራል።

# የብዝሃ ቋንቋ ተማሪ ምዝገባ

# አጠቃላይ የ ML+FML ምዝገባ ከ 5 አመታት በፊት ከነበረው በ 10% የቀነሰ ሲሆን ነገር ግን ካለፈው አመት ጋር በሚነጻጸር ቲዜ በ 2% ጨምሯል







# አጠቃላይ ML አሁንም ከቅድመ-ወረርሽኝ ደረጃዎች በታች ሲሆን ነገር ግን ELD 1-3S ካለፈው አመት አንስቶ በ ~1,300 ተማሪዎች እድገት አሳይቷል





# በ SY2122 በርካታ አዳዲስ ተማሪዎች ELD 1-3S ጭማሪ ያሳየ ሲሆን እንዲሁም ጥቂት ተማሪዎች የ ELD ደረጃዎችን በማደግ ላይ ይገኛሉ





# በ SY2122 በርካታ አዳዲስ ተማሪዎች ELD 1-3S ጭማሪ ያሳየ ሲሆን እንዲሁም ጥቂት ተማሪዎች የ ELD ደረጃዎችን በማደግ ላይ ይገኛሉ




*Excludes students that exited the district between June and October*

# የ ML ምዝገባ በፕሮግራም አይነት



# በ ELD 1-3S ያለው የ ML ፕሮግራም ምዝገባ በዚህኛው አመት ወደ ቅድመ ወረርሽኝ ደረጃዎች መመለስን አሳይቷል



# የSEI ምዝገባ እድገት የታየው በዋነኛነት በስፓኒሽና በብዝሃ ቋንቋ ፕሮግራሞች ላይ ነበር





# ከቋንቋ ቡድን አንጻር የ ML ምዝገባ



# በ ELD 1-3S ውስጥ የነበረው የእድገት ደረጃ በጥቂት የቋንቋ ስብስቦች መካከል ትኩረቱን ያደረገ ነበር

**ከቋንቋ ቡድን አንጻር የጥቅምት ELD 1-3 ምዝገባ**

| የቋንቋ ቡድን | SY1718 | SY1819 | SY1920 | SY2021 | SY2122 | SY2223 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አረብኛ | 213 | 186 | 189 | 133 | 131 | 180 |
| ቨርዴያን ክሪኦል | 762 | 816 | 737 | 691 | 623 | 632 |
| ቻይንኛ | 550 | 435 | 421 | 349 | 377 | 357 |
| እንግሊዝኛ | 841 | 1010 | 1055 | 1261 | 1355 | 1456 |
| ፈረንሳይኛ | 52 | 49 | 44 | 33 | 50 | 60 |
| ሃይቲያን ክሬኦሌ | 763 | 767 | 666 | 555 | 525 | 607 |
| ሌላ | 299 | 279 | 277 | 268 | 265 | 320 |
| ፖርቹጋልኛ | 221 | 212 | 279 | 286 | 339 | 494 |
| ሶማሊኛ | 145 | 119 | 113 | 94 | 80 | 75 |
| ስፓኒሽኛ | 5616 | 5882 | 5634 | 5694 | 5851 | 6704 |
| ቬትናምኛ | 468 | 430 | 373 | 390 | 342 | 322 |

# MLS+FMLS ከአካል ጉዳተኝነት ጋር



# አካል ጉዳተኞች ከ MLS+FMLS ጋር ከባለፈው አመት በ 11% እድገት ያሳየ ሲሆን አሁን ላይ ደግሞ ከቅድመ ወረርሽኙ ደረጃዎች ጋር ተመሳሳይነት አለው

## Total MLs+FMLs with Disabilities




*Includes students with resource room, inclusion, or substantially separate IEPs*



# የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች በ MLS እና FMLS መካከል ያለው ምዝገባ ከባለፈው አመት አንጻር በ 12 በመቶ እድገት አሳይቷል




*Includes students enrolled in Inclusion or Substantially Separate Programs*



# በ MLS+FMLS መካከል ያለው የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ምዝገባ

## እድገት በ ELD 1-3S የተመራ ነበር





## በልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ከተመዘገቡት የሁሉም MLS+FMLS በመቶኛ ከ MLS ያነሰ ቢሆንም ነገር ግን ከ ELD 1-3S መካከል ከፍተኛው



# እባሪ፡ ከታህሳስ በጀት አቀራረብ እስከ SC



# ቀደም ብለው ከነበሩት 6 አመታት ከአጠቃላይ የ BPS ምዝገባ በ 7,667 ተማሪዎች (14%) ቅናሽ አሳይቷል




- አጠቃላይ ምዝገባው ቀደም ብለው በነበሩት ስድስት አመታት የቀነሰ ሲሆን ትልቁ የአንድ አመት ቅናሽ የታየው በወረርሽኙ ወቅት ነው።
- ዘንድሮ በ 545 ተማሪዎች ያህል ምዝገባው የቀነሰ ሲሆን ይህም ከተጠበቀው በታች የነበረና ለዚዚህም ዋነኛው ምክንያት የእንግሊዘኛ ተማሪዎች ፍልሰት ነው።

## የ BPS ምዝገባ ሁኔታዎች



# የ BPS ምዝገባ ሁኔታዎች

## ቀደም ብሎ ከነበረው የትምህርት ዘመን በ 690 ተማሪዎች ያህል የተማሪዎች ቁጥር ያደረ ሲሆን ይህም በዚህ አመት ከሚጠበቀው ዝቅ ያለ ቅናሽ አሳይቷል




- ከጥቅምት 2021 እስከ ሰኔ 2022 ባለው ጊዜ ውስጥ በ 690 ተማሪዎች እድገት ያሳየ ሲሆን ይህም ባለፉት 10 አመታት ውስጥ ትልቁ የመካከለኛው አመት እድገት ነው።
- የዚህ እድገት መነሻው በእንግሊዘኛ ተማሪዎች ፍልሰት ነው።



# የአንደኛ ደረጃ ክፍሎች ከፍተኛ መቀነስን ያሳየ ሲሆን ይህም የወደፊት ሊኖር የሚችል መቀነስን ያመለክታል




- ቀደም ብለው በነበሩት 6 አመታት ከ K2 እስከ 5ኛ ክፍል ያለው ምዝገባ በ 4,928 ተማሪዎች (19%) የቀነሰ ሲሆን ይህም በዋነኛነት ወደ ስርአቱ በገቡት አነስተኛ ቡድኖች የተነሳ ነው።
- ለወደፊት ለሚኖር ምዝገባ ጥሩ የሚሆነው አመላካች የአሁን ላይ ያለው ምዝገባ ሲሆን ከዚህም አኳያ የሁለተኛ ክፍል ምዝገባ ወደፊት መቀነስ ሊታይበት ይችላል።

## የ BPS ምዝገባ ሁኔታዎች



# የአንደኛ ደረጃ መቀነሶች መነሻው በስርአቱ ውስጥ የሚገቡና የሚንቀሳቀሱ በዛው የተወለዱ አነስተኛ ነዋሪዎችና በአነስተኛ K2 ክፍሎች ላይ ነው




- በቦስተን በተወለዱ ነዋሪዎችና በ BPS K2 ተማሪዎች ብዛት መካከል ከ 5 አመት በኋላ ወጥነት የሚታይበት ግንኙነት አለ።
- በ 2011 እና 2019 መካከል በቦስተን በተወለዱ ነዋሪዎች በ 10% መቀነስ ታይቷል።

የ BPS የምዝገባ ሁኔታዎች



# ይህ የ BPS ላይ ብቻ ያጋጠመ አይደለም - በ 8 ዓመታት ውስጥ የ K2 ቦስተን ነዋሪ ምዝገባ በ 22% ቀንሷል




- በ SY1314 እና SY2122 መካከል የቦስተን ነዋሪዎች የ K2 ምዝገባ በ 1,228 ተማሪዎች ወይም 22 በመቶ የቀነሰ ሲሆን ይህም በወረርሽኙ ወቅት ከፍተኛው ቅናሽ እንደሆነ አመላክቷል።
- የ K2 ምዝገባ ገና እንዳልተመለሰ የሚጠቁም ሲሆን ይህም የወረርሽኝ ተጽእኖ ብቻ ላይሆን ይችላል።
- በ 5 አመታት ውስጥ በሁሉም ክፍሎች የቦስተን ነዋሪ ምዝገባም በ 10% የቀነሰ ሲሆን ይህም ከ 79,016 በ SY1617 ወደ 71,515 በ SY2122 ነው።

## የ BPS የምዝገባ ሁኔታዎች



# የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ምዝገባ እድገት ያሳየ ሲሆን ይህም ወደ ከፍተኛ አጠቃላይ የፍላጎት ክምችት በማምራት ላይ ነው




**Includes Inclusion and Substantially Separate Programs*

የ BPS የምዝገባ ሁኔታዎች

- ቀደም ብለው በነበሩት 8 አመታት የልዩ ትምህርት መርሃ ግብሮች በ10% ያደገ ቢሆንም የሌሎቹ ፕሮግራሞች ምዝገባ ግን በ 17% ቅናሽ ታይቶበታል።
- ይህም በዲስትሪክቱ ከፍተኛ የሆነ አጠቃላይ የፍላጎት ክምችት እንዲፈጠር አድጓል።